ብልፅግና ፓርቲ
PROSPERITY PARTY

“ከቃል እስከ ባህል”

# ሁለተኛው የብልፅግና መደበኛ ጉባዔ ውሳኔዎችና አቅጣጫዎች

የካቲት 2017

ሆሳዕና

# ይዘት




1. መግቢያ
2. የጠንካራ ፓርቲ ግንባታን አጠናክሮ መቀጠል
3. ብሔራዊነት ገዥ ትርክት ግንባታ ማጠናከር
4. ውጤታማ የሰላም ግንባታ ሥራ መስራት
5. የፍትህ ዘርፍ ውጤታማነትን ማሳደግ
6. የሀገር ግንባታ/ Nation Building ማጠናከር
7. ኢኮኖሚ ልማትን ማፋጠን
8. ማህበራዊ ብልጽግናን የሚያረጋግጡ ሥራዎችን በውጤታማነት ማስቀጠል
9. ውጤታማ የዲፕሎማሲ ሥራዎችን መስራት
10. የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም ውጤታማነትን ማረጋገጥ
11. ጠንካራ የሚዲያና ኮሙዩኒኬሽን ሥራ መስራት
12. ማጠቃለያ

# 1. መግቢያ

1. ሁለተኛው የብልፅግና ፓርቲ ጠቅላላ ጉባኤ ከጥር 23-25 ቀን 2017 ተካሂዷል።

2. በጉባኤ ከሁሉም የሀገሪቱ ብሔር ብሔረሰቦች፣ አካባቢዎች፣ እምነቶች፣ የማኅበረሰብ ክፍሎች፣ የእድሜና የጾታ ስብጥሮች እንዲሁም በውጭ ከሚኖሩ ወገኖች የተወከሉ 1681 አባላት ተሳትፈዋል፡፡

3. ጉባዔያችን በመጀመሪያ ጉባኤ፡-

- የፖለቲካ ምኅዳሩን ለማስፋት፤
- ዘላቂ ሰላምን ለመገንባት፤
- ኢኮኖሚ ዕድገትን ለማሻሻል፣
- ስብራቶች ለመጠገን፣
- ገቺ ትርክትን ለማስረጽ፣
- በምግብ ራሳችንን ለመቻል፤
- የባሕር በር ጉዳይን ዋና አጀንዳ ለማድረግ፤
- የተጀመሩ ሜጋ ፕሮጀክቶችን ለማጠናቀቅ፤
- አረንጓዴ ዐሻራን ባህል ለማድረግ፤
- ፍትሐዊ የመሠረተ ልማት ተግባራትን ለማሣለጥ፤
- ማህበራዊ ልማት ተደራሽነት ለማረጋገጥ
- ብሔራዊ ጥቅምን ለማስከበር



4. ጉባኤ በሠራቸው ሥራዎች፣ በሀገራችን ወቅታዊ ሁኔታ፣ ሀገራችን በገጠሟት ፈተናዎች እና ባሳካቻቸው ድሎች ዙሪያ በዝርዝር መክሯል፡፡

ብልፅግና ፓርቲ
PROSPERITY PARTY

**በሁለተኛው የብልፅግና ፓርቲ ጉባኤየተወሰኑ ውሳኔዎች እና የተቀመጡ አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል።**

# 2. የጠንካራ ፓርቲ ግንባታን አጠናክሮ መቀጠል

የአመራርና የአባላት ብቃትና ጥራት የማሳደግ በተጠናከረ መልኩ የሚሰራ ይሆናል።

አባላትንና አመራርን ለማጥራት የሚያስችል ውጤታማ የምዘናና የግምገማ ሥርዓት እንዲዘረጋ ይደረጋል፡፡

የሥነ ምግባርና የሞራል ዝቅጠት ተጠቂ በሆኑ አመራሮችና አባላት ላይ የማረም ተግባር በቀጣይነት ይከናወናል፡፡

አዳዲስ አባላትን የመመልመል ሥራ በጥራትና በብቃት እንዲፈጸም ይደረጋል።



የአመራሩንና የአባላቱን የአመለካከት እና የተግባር ጽናት የሚፈጥሩ፤ መዋቅራዊ ጥንካሬን የሚያመጡ እና የውስጠ ፓርቲ ዴሞክራሲን የሚያጠናክሩ ሥራዎች በቀጣይነት ይሰራሉ፡፡

ጠንካራ የአደረጃጀት፣ የአሠራር እና የፋይናንስ ዐቅም እንዲፈጠር ይሰራል፡፡

ከማዕከል እስከ ወረዳ ዲጂታላይዜሽንን ይተገበራል።

የፓርቲያችን ኢንስፔክሽን እና ስነምግባር ኮሚሽን ማጠናከርና የሚሰጣቸውን ግብረ መልሶችን በአግባቡ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

# 3. ብሔራዊነት ገዥ ትርክት ግንባታ ማጠናከር



- ብሔራዊነት ገዥ ትርክት ሆኖ በልሂቃን እና በሕዝቡ ዘንድ እንዲሠርጽና ኅብረ-ብሔራዊ አንድነታችን እንዲጠናከር ፓርቲያችን ብልጽግና የመሪነት ሚናውን እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

- በማኅበረሰባችን መካከል መግባባትን የሚፈጥሩ ልዩ ልዩ ሕዝባዊ ውይይቶች በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎችና በሁሉም አማራጭ መንገዶች እንዲከናወኑ ይደረጋል፡፡

- በተለያዩ ማኅበረሰቦች መካከል የሕዝብ ለሕዝብ ውይይቶችን በማድረግ የብሔራዊነት ገዥ ትርክት እንዲሠርጽና በሕዝቦች መካከል ትሥሥርና ኅብረ ብሔራዊ አንድነት እንዲፈጠር ይሰራል፡፡

# 4. ውጤታማ የሰላም ግንባታ ሥራ መስራት



- በጉባኤ ለሕዝብ የገባነው ቃልኪዳን ግጭትን ማስቀረት እና መረጋጋት መፍጠር እውን እንዲሆን እንሰራለን።
- ግጭትን ለማስቀረት እና መረጋጋትን ለመፍጠር የፀጥታ ተቋማት አቅምና የሕዝቡን ተሳትፎ እናጠናክራለን።
- ሁሉም ኃይሎች ወደ ሀገራዊ ምክክር እንዲመጡ የሚጠበቅብንን ሁሉ እንደ አማራር፣አባል እና ዜጋ በጋራ የምንወጣ ይሆናል።
- ግጭቶች በውይይት፣ በድርድርና ብሔራዊ ጥቅምን ማዕከል ባደረገ መንገድ እንዲፈቱ እንደ መሪ ፓርቲ አስፈላጊው ሁሉ ይከናወናል።
- ለአዎንታዊ ሰላም ግንባታ ማህበራዊ ፍትህን የሚያረጋግጥና ለሁሉም እኩል እድል የሚሰጥ፣ ኢኮኖሚያዊ ልማትን ለማረጋገጥ የሚያስችል፣ ሰብአዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን የሚያስከብር፣ ትላንት፣ ዛሬን እና ነገን የሚያስተሳስርና ህብረ-ብሔራዊ አንድነትን የሚያጠናክር ዘላቂ አቅጣጫን እንከተላለን
- የህግ የበላይነትን የሰፈነበት ሀገራዊ አውድ እንዲፈጠር ይደረጋል።
- ጠንካራ እና ገለልተኛ የፍትህ ስርዓት መገንባት፣ የህግ አስከባሪ አካላትን የማጠናከር ሥራ ይሠራል።
- የመንግስት ተቋማት ውጤታማ እና ተጠያቂ እንዲሆኑ የማድረግ እና የሲቪል ማህበረሰብን ተሳትፎ የማሳደግ ሥራ ይሠራል።

- ሀገራዊ ምክክሩ ውጤታማ እንዲሆን ማስቻል፣ የሰላም ንግግሮችን በስፋት መፍጠር፣ የፀጥታ ተቋማት አቅም እና ብቃት ማሳደግ የሽግግር ፍትህ እና ተግባራዊነት እና ስኬታማነትን ማረጋገጥ

# 5. የፍትህ ዘርፍ ውጤታማነትን ማሳደግ




የህዝባችንን የፍትህ ጥማት የሚያረካ ዜጎች የሚተማመኑበት የፍትሕ ሥርዓት መፍጠር ላይ ርብርብ ይደረጋል፡፡

የፍትሕ ሥርዓቱን የማዘመን፣ ብቁ ባለሞያዎችን የመመደብ፣ ፈጣንና አስተማማኝ አገልግሎት እንዲሰጥ የማስቻል፣ የፍትህ አካላት ነጻነትንና ተጠያቂነትን በሚዛን የማረጋገጥ ተግባራት የሚከናወኑ ይሆናል፡፡

የፍትሕ ሥርዓቱ ቀልጣፋና ውጤታማ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

የፍትሕ ተቋማትን ምቹ፣ ዘመናዊ እና በቴክኖሎጂ የተደገፉ እንዲሆኑ ይደረጋሉ፡፡

በዘርፉ ሌብነትን የመታገል ሥራዎች መርህን በጠበቀ አኳኋን በትኩረት የሚሰራ ይሆናል፡፡

# 6. የሀገር ግንባታ ማጠናከር/ Nation Building/

ትውልዱ መቻቻልን፣ ኅብረ ብሔራዊ አንድነትን፣ ወንድማማችነትን/ እኅትማማችነትንና አርበኝነትን እየተማረ እንዲያድግ ይደረጋል።

የዴሞክራሲ ተቋማትን የማጠናከር ሥራ በቀጣይነት ይሰራል

ሀገራዊ ምክክር የተሳካ እንዲሆን ይደረጋል።

ዴሞክራሲን በተቋምና በባህል በመገንባት ረገድም ዴሞክራሲን በደረጀ ተቋማዊ አቅም ወደ ሥርዓታዊ ልህቀት እንዲሸጋገር ይሰራል።



የሽግግር ፍትሕ ሥርዓት ሀገራዊ ሰላምን ዘላቂ ለማድረግ በሚችልበት አግባብ እንዲፈጸም ይደረጋል።

የዴሞክራሲ ባህል ግንባታን ማጠናከር፣ የነፃነት አስተዳደርን ማጎልበት፣ መብትና ግዴታን በሚዛን የሚያይ ማህበረሰባዊ አውድ መፍጠር እና የህግ የበላይነትን ማስከበር በትኩረት የሚሰሩ ይሆናል።

አጎራባች ክልሎች ለሀገር ግንባታ ከፍተኛ ፋይዳ ባለው መልኩ በጋራ ጉዳዮች ላይ ተናበውና ተቀናጅተው እንዲሰሩ ይደረጋል።

ነጻ፣ ገለልተኛና ብቃት ያላቸውን ተቋማት በማባዛት የሀገረ መንግሥት ግንባታ ሥራችንን በጠንካራ መሠረት ላይ ለማቆምና ጠንካራ የዴሞክራሲ ባህል ለመፍጠር አበክረን እንሠራለን።

# 7. ኢኮኖሚ ልማትን ማፋጠን

የኢኮኖሚ ዘርፎች የተጀመረውን ዕደገት ለማስቀጠል ምርትና ምርታማነትን የማሳደግ ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል።

ኢኮኖሚያችን መዋቅራዊ ለውጥ እንዲያመጣ በማስቻል በሚቀጥሉት 3 አመታት በአማካይ 8.4% እድገት ለማስመዝገብ እንሰራለን።

ለውጪ ንግድ የምናቀርባቸውን ሸቀጦች በዓይነት፣ በመጠንና በጥራት እንዲጨምሩ ይሰራል።

የኑሮ ውድነትን የሚያረጋጉ የልማት መርሃ ግብሮች እና ሌሎች እርምጃዎች ትርጉም ያለው ውጤት በሚያመጣ መልኩ እንዲፈፀሙ ይደረጋል።

የበጀት ጉድለት ከሀገራዊ ጠቅላላ ምርት ጋር ሲነጻጸር ከ3 በመቶ እንዳይበልጥ ይደረጋል።

ዘላቂ የስራ እድል በመፍጠር ረገድም ለ9.15 ሚሊዮን ዜጎች ዘላቂ የስራ እድል ይፈጠራል።

በግብርናው ዘርፍ ሁሉንም ባለድርሻ አካላት በማስተባበር የምግብ ዋስትናን እናረጋግጣለን።

በኢንደስትሪው ዘርፍም ምርትና ምርታማነት ማላቅ፣ የምርት ጥራትን ማሳደግ፣ለአካባቢ ተስማሚ ኢንዱስትሪዎችን የማስፋፋት ሥራ ይሰራል።

የዲጂታል ኢኮኖሚን የማበልጸግ ሥራ ይሰራል።

የኮሪደር ልማት ሥራን አጠናክረን እናስቀጥላለን።

በቱሪዝም ዘርፍም የቱሪዝም መዳረሻዎችን በአግባቡ መለየት፣ ማልማትና ማስፋፋት፣ የቱሪዝም ፕሮሞሽን ይደረጋል።

# የኢኮኖሚ ልማት በግብርናው ዘርፍ...



- የመስኖ ቅምን የማጎልበት
- የአሲዳማ መሬቶችን ማከም
- ግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎትን የማጠናከር
- ያሉን የምርት ወቅቶች ወደ ሦስትእና አራት ጊዜያት የማሳደግ
- ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ዘላቂ ግብርና ልማት የማካሄድ
- የአረንጓዴ አሻራ መርሃ-ግብር ትግበራ በላቀ የሕዝብ ተሳትፎና ባለቤትነት በውጤታማነት እንዲቀጥል ይደረጋል
- ለኢንዱስትሪና ለወጪ ንግድ በቂ ምርት የማቅረብ

# 8. ማህበራዊ ብልጽግናን የሚያረጋግጡ ሥራዎችን በውጤታማነት ማስቀጠል

ጥራት ያለው ትምህርት ለትውልድ ሁለንተናዊ ልህቀት ወሳኝ ግብዓት መሆኑን ከግምት ያስገቡ ሥራዎች በውጤታማነት የሚፈፀሙ ይሆናል።

"ትምህርት ለትውልድ" በሚል የተጀመረውን መርሃ ግብር አጠናክሮ በማስቀጠል ት/ቤቶች ለመማር ማስተማር እና ለትምህርት ጥራት መረጋገጥ ምቹ እንዲሆኑ በሰፊው ይሰራል።

ትውልዱ መቻቻልን፣ ኅብረ ብሔራዊ አንድነትን፣ወንድማማችነትን/እኅትማማችነትንና አርበኝነትን እየተማረ እንዲያድግ በትኩረት ይሰራል።

በሽታን ቀድሞ የመከላከልና አክሞ የማዳን ሥራዎች ለጤናማና አምራች ትውልድ ግንባታ የሚያበረክቱትን አስተዋጽኦ ወደ ላቀ ደረጃ የሚያደርሱ ሥራዎች በቀጣይነትይፈፀማሉ።

የጤና መድኅን ተጠቃሚዎችን የማበራከት፣ ሆስፒታሎችንና የጤና ጣቢያዎችን የማስፋፋት እና የጥራትና የተደራሽነት የማሻሻያ ርምጃዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ይደረጋል።

የሕጻናትን እና የአረጋውያንን ሁለንተናዊ መብት እና ጥቅም የሚያስከብሩ፣ የአካል ጉዳተኞችን ሁለንተናዊ መብት፣ ክብርና ደኅንነት የሚያስጠብቁ፣ ዐቅመ ደካሞችን እና ለችግር ተጋላጭ የሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎችን የሚደግፉ ሥራዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ።

የወጣቶችና ሴቶች ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነትየሚያረጋገጡ ሥራዎች በትኩረት ይሰራሉ።

# 9. ውጤታማ የዲፕሎማሲ ሥራዎችን መስራት

ሀገራዊ አንድነትን
የሚያጠናክር
የዲፕሎማሲና የውጭ
ግንኙነት አቅጣጫን
በመከተል ብሔራዊ
ጥቅማችንና
ክብራችንን ከፍ የሚያደርጉ
ሥራዎችን በትኩረት
እንሰራለን፡፡




በውጭ ሀገራት የሚኖሩ
ዜጎቻችንን ደኅንነትና ክብር
የማስጠበቅ ሥራዎችን
በውጤታማነት እናስቀጥላለን

የባሕር በር ጥያቄ
ሰላማዊና
ዲፕሎማሲያዊ መፍትሔ
እንዲያገኝ በሙሉ
ዐቅማችን በቁርጠኝነት
እንሰራለን

ዲፕሎማሲያችን
ከመሽኮርመም ወጥቶ
የኢትዮጵያን ብሔራዊ
ጥቅምና ፍላጎት
መርሕንና እውነትን
መሠረት ባደረገ
ለማስከበር አበክረን
የምንሰራ ይሆናል

# 10. የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም ውጤታማነትን ማረጋገጥ

በየደረጃው የሚተገበር፣ ውጤታማነቱ የተረጋገጠ፤ በዘመናዊ የቴክኖሎጂ ዐቅም መሪነት የተሣሠረና ከሌብነት እና ከብልሹ አሠራር የተላቀቀ ሲቪል ሰርቪስ ለመገንባት ተቋማዊ ባህሪን መሠረት ያደረገ፣ ገቢር ነበብ ሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል።



የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም በብቃት፣ በጥራት እና በተያዘለት ጊዜ ተከናውኖ ሕዝባችን የሚገባውን አገልግሎት ለማግኘት እንዲችል በየደረጃው ያለ አመራር በትኩረት እንዲመራው ይደረጋል።

የሠራተኛ ሥነ ምግባር እና ብቃት የሚያሳድጉ፣ ሲቪል ሰርቪሱ አትዮጵያን መስሎ እንዲደራጅ የሚረዱ፣ ተቋማትን በዲጂታል መረብ የተሳሰሩ እንዲሆኑ፣ ሠራተኛው ለሥራው ተመጣጣኝ ክፍያ እንዲያገኝ የማድረግ ሥራ ምልአተ ህዝቡን በማሳተፍና ሌት ከቀን በመትጋት የሚሰራ ይሆናል።

የሕዝብ ቅሬታ ምንጭ የሆኑ አገልግሎት ሰጪ ዘርፎች ላይ በልዩ ጥናት የአገልግሎት ማስተካከያ ለማድረግና የሕዝቡን ርካታ ለማሳደግ በቁርጠኝነት ይሠራል።

# 11. ጠንካራ የሚዲያና ኮሙዩኒኬሽን ሥራ መስራት



- ዘመኑ መረብን የሚመጥን የሚዲያ እና የኮሙኒኬሽን ሥራ ይሰራል።

- አፍራሽ ተልዕኮ ይዘው ሚዲያውን ለግጭት፣ ለብጥብጥና ለወንጀል በሚጠቀሙት አካላት ላይ ሕግ የማስከበር ሥራ ይሠራል።

- የብልጽግና አመራሮችና አባላት መላውን ሕዝብ በማሳተፍ፣ ማኅበራዊ ሚዲያውን ለገዥ ትርክት ግንባታ፣ ለኅብረ ብሔራዊ አንድነት፣ ለዕውቀት ሽግግር እና የኢትዮጵያን እውነት ለመግለጥ እንዲጠቀሙበት የማድረግ ሥራ ይሰራል።

# 12. ማጠቃለያ

ከጉባኤ እስከ ጉባኤ ያስመዘገብናቸው ሁሉም ድሎች የተገኙትም ሕዝቡ በፓርቲያችን ላይ ባሳደረው እምነት፣ በሰጠው ድጋፍና ባደረገው ተሳትፎ ልክ ነው። እስከ ቀጣዩ ጉባኤው ድረስም ሕዝቡን በሁሉም ሀገራዊና ከባቢያዊ አጀንዳዎች ዙሪያ በንቃትና በስፋት ለማሳተፍ በልዩ ትኩረት በቁርጠኝነት የሚሠራ ይሆናል።

የትግል ጉዞችንን የሚፈትኑ አንድም ከነባሩ የፖለቲካ ባህል የሚመነጩ ፈተናዎች፣ ሁለትም አዲሱ ዘመን በራሱ የሚፈጥራቸው አዳዲስ ፈተናዎች መኖራቸውን ተገንዝበንና ፈተናን ወደ ዕድል የመቀየር ልምዳችንን ተጠቀምን ሁል ጊዜም ወደ ፊት መጓዝ የግድ ይላል።

አይቀሬ የሆኑ ፈተናዎችን በመሻገርም ሆነ ሁለተኛው የብልፅግና ፓርቲ መደበኛ ጉባዔ ውሳኔዎችና አቅጣጫዎች በሚገባ ተግባራዊ በማድረግ ረገድ በየደረጃው የሚገኙ የብልፅግና አመራሮች፣ አባላት እና ደጋፊዎች በቆራጥነት መረባረብ ይኖርባቸዋል።

መላው ሕዝባችንም ለውጤቱ አብሮን እንደከዚህ ቀደሙ ሁሉ እንደሚሰለፍ እናምናለን። የተፎካካሪ ፓርቲዎች አመራሮችና አባላትም ኢትዮጵያን ለማበልጸግ በጀመርነው ጥረት የሚጠበቅባቸውን እንደሚያደርጉ ተስፋ እናደርጋለን።

የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ ብልጽግና እውን ለማድረግ የጀመርናቸውና በሕዝብ ንቅናቄ ስንሰራቸው የቆየናቸው ዘርፈ ብዙ መርሃ-ግብሮች የታለመላቸውን ዓላማ በዘላቂነት ያሳኩ ዘንድ ተቋማዊ/ሥርዓታዊ፣ ሕዝባዊና ዘላቂ ሆነው ወደ ባህል እንዲቀየሩ መላው ሕዝባችን ከፓርቲያችንና ከመንግሥታችን ጎን እንዲሆን ጥሪያችንን በአክብሮት እናቀርባለን።

ብልፅግና ፓርቲ
PROSPERITY PARTY

# አመሰግናለሁ!